# የተዳፈነ እሳት የጠፋ ይመስላል
# በኢሕአፓ ላይ ዘመቻው ተጧጧፈሳ!

ክፍል 1

ኢሕአፓ ጠፍቷል፣ተኗል፣ ሞቷል በሚል ደርግና አሽከሮቹ ይደነፉ በነበረበት ወቅት እሳተ ገሞራው ሐይሉ ገብረ ዮሓንስ የምትቀጥለውን በ 1983 " እሳት ጠፋ! ይበል? በሚል ርዕስ ከትቦልን ነበር፤

*ስንቱን ፈተና አልፎ በሚይስደንቅ ትግሥት*

*በትግሉ ድቁና ሆነ ቅስና፤ኋላም በምንኩስናው ዘመናት*

*ከፍተኛ ደረጃ ደርሶ ሲዘጋጅ ለብቃት*

*ዛሬ ቢያወሩልኝ አልሰማም የሸገተ ወሬ የቀመለ*

*ድፍን አበሻ ቢቀላምድ እንዲህ እንዲህ ኢያለ*

*ጉዳሙን ትቶ ኮበለለ*

*"ይህ አባ ቆቡን ጣለ !!"*

ኢህአፓም ትግሉን ቶት አልከሰመ፤ ገሞራውም በሆድ አምላኪዎችና ፈሪዎች ቢከዳም እስከ ዕለት ሞቱ ጻረ ወያኔ ትግሉን አላቆመ ። እሳት አልጠፋ አለና ታዲያ የደርጉ ሲያበቃ የወያኔ ዘረኛ ሰደድ አሁንም በኢሕአፓ ላይ ተነሳ ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ጻረ ኢሕአፓው ዘመቻ በየቦታው ተፋፍሟል ። ለምን ብሎ መጠየቅ ራሱ የለም ተብዬው ድርጅት ለወያኔ ውጋት ሆኖ መቀጠሉን አብሳሪ ነው ። ወያኔ ከየህጋዊ ድርጅቶች ኢሕአፓ ያላቸውን እየመነጠረ መቀጠሉ ደግሞ ምስጢር አይደለም ። በአሁኑ ጊዜ ጠንክሮ የመጣው ዘመቻ በሀገር ቤትም ከውጭ ሀገርም ነው ። ከአሜሪካና አውሮጳ ወደ ሀገር ቤት እየደወሉና ገንዘብ ሞልቷልና ገላ ሰደው ለሰዓቶች የሚያወሩት የወያኔ አዳናቂዎች በኢሕአፓና በአመራሩ ላይ ሰፊ ሀሰትን እያሰራጩ ናቸው ። ውሸትን በተመለከተ ገሞራው በዚሁ የግጥም መጽሃፋ የሚከተለውን አስፍሮ ነበርና መጥቀሱ ጠቀሜታ አለው ።

*" ነገረ-ውሸት በዓለም አቀፍ ደረጃ ጭምር የሚያውደለድል ችግር እንደ መሆኑ በዘመናችን የነገር ልቦናን (ሳይኮሎጂስቶች) ምሁራን እንዳጦዘ አለ ። የነገረ ሐሰትን ውስብስብ ባህርይና የመነሻው ጥቅንጥቁንም ሊመረምሩት በተነሱ ቁጥር የራሳቸውንም አዕምሮ ሳይቀር እንዳናወዘው አለ ። ሀሰት በጊዜ ይዘት አንጻር ስሉስ ወቅቶችንም ይጠቀምባቸዋል ። በመሆኑም የጊዜ ገደብ ኢያውቅም። በሬ ወልዶ ነበር፤ በሬ እየወለደ ነው ፤ በሬ ይወልዳል በሚል የቱልቱላ ጥሩምባው ስላለፈው ይወሸክታል ። ባሁኑም ጣቃውን ይቀዳል፤ በወድፊቱም ላይ ይቀጥፋል ። ውሸት በሁለንተናው ጻረ ሀቅ ነው ። በግለሰቦችም ሆነ በማህበረሰቦች ኑሮ ውስጥ የድከመት ሸንቁር ቀዳዳ ፈልጎ በመግባት*

*አለያም ለስላሳ የህይወት ክፍሎችን ሰርስሮና ሰርጎ በመግባት ያላፈረሰው ትዳር፤ ያልናደው ንብረት፤ያልመዘበረው ወዳጅነት አይገኝም ።ሌላው ቀርቶ እንደ ፍቅር ባለው ትልቅ የስሜት ወዳጃዊ ግንኙነቶች ውስጥ ጣልቃ ገብቶ ሱክ በማለት፤ ፍቅረኞችን ጭምር ሲያናቁር ኖሯል። ልባዊ ዝምድናን ፈጥረው ትዳርን  ያህል ባለቃል ኪዳን ውል መስርተው፤ ንብረት አደርጅተው፤ወልደው፤ ከብደው ለዘመናት ተከባብረው የኖሩ አባት እናቶችን ሳይቀር ውሸት በመሃላቸው ገብቶ በማናወጽ የሞቀ ትዳራቸውን በማተራመስ እንዳልልነበር ሲያደርገው በየደጋጋሚ ታይቷል ። በዚህ አጸያፊ ተግባሩ በየማህበረሰቡ አባላት ሁሉ ርኩስ ውሸት ሲወገዝና ሲኮነን ኖሯል ።"*

ቢወገዝ ቢከሰስም ውሸት ተነቃብኝ ብሎ የሚተን ሳይሆን ራሱን በመደጋገም ሃቅን መስሎ ሊያወናብድ ይጥራል ። ውሸታችሁ ተነቅቶበታል በቃ ሲባሉ እምቢኝ አሻፈረን ብለው የደረቁ ወያኔዎችና የደርግ ርዝራዦችን ዛሬ ይመለከቷል፡ ገሞራው ትንተናውን በመቀጠል የሚከተለውን አፍሮ ነበር ።

*" በየፖለቲካው መስክ የሚቧረቅ ውሸት የራሱ ዓይነትና ይዞታው ባህርይ ሲኖረው በአብዛኛው ሥልጣንና ሃይላዊ ጉልበት ላይ በማነፋነፍ የሚሽከረከር ውሸት ነው ። ለሥልጣን የሚቋምጥ ግለ-ሰብ ወይም ቡድን "ከእኔ በላይ ለአሳር ነው" በሚል ዘዴ "ከሰማይት የወረድኩ ልዩ ፍጡር ነኝ" እስከማለት ድረስ ያስቀባጥረዋል ።ከመሰሉ ፍጥጡርም የተለየ ልዩ ሰው ለመምሰል " ደሜ ሓምራዊ ነው " ብሎ እስከመዘላበድ ድረስ ያቃዠዋል ።ትውልዴም ባለ ሺ ጅማት ካላቸው ከነእንቶኔ ዝርያ፤ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ነው እስከማለትም ድረስ ያስቀላምደዋል ። ለዝህ ዓይነትየባለ ውሸት አበጋዝ ብዙ ስመ ጥርና ዕውቅ አምባገኖችን በናሙናነት ማቅረብ ይቻላል።...ትንሽ ዘርዘር አድርገን በዘመናችን የሚከናወኑትን ዓይን አውጣ ውሸቶችን ብንጠቃቅስ ከፖለቲካ ጋር የቅርብ ዝምድና ያለውን የፕሮፓጋንዳ ውሸት መጥቀሱ እጅግ አርኪ ነው ። ባልነበረ ጦር ሜዳና ባልዘመተ ሰራዊት ባዶ ሁኔታ ላይ የድል ቅዠት ያወፈፈው ቡድን ድንገት ተነስቶ ሺ ሰዎች ማረክሁ፤ዘመናይ መሳሪያዎችን በገፍ ማረክሁ፤ሺ ገደልኩ፤ ጉጡርጡራ የተባለውን ልዩ ለጦርነት አመቺ ቦታ ከጠላት አስለቅቄ ከእጄ አገባሁ በማለት ደረቅ ቱልቱላውን ይነፋል ።የሚገርመው ደግሞ የራሱ ተዋጊዎች ልዩ የአቅቤ ርዕስ ጥይት የማያስመታ መድሃኒትና አስማት ያላቸው ይመስል ከዚህ ሁሉ ወራሪ ሰራዊት ውስጥ ያን ያህል ከፍተኛሲያደርግ አንድ እንኳን መሞት ቀርቶ ያልቆሰለበት መሆኑን አለመግለጹ ነው ። ይህ ዓይነት የጦርነት ግብግብ ውሸት  በዘመኑ ቋንቋ ጸሊም ፕሮፓጋንዳ ወይም አሳሳች ዜና ተብሎ ይጠራል።አስር ተዋጊዎችን ምርኮ አስገብቶ እንደሆነ አስሩን በአስር ያባዛና፤ መቶ ተዋጊዎች ማርኬያለሁ ሲል ይፋሽካል። የትልቅ ከተማ ጎረቤት የሆነች የገጠር መንደር የያዘ እንደሆነ ዋናውን ከተማ በቁጥጥሬ ስር አድርጊያለሁ ሲል ጣቃውን ይቀዳል ። ከዋሹ አይቀር እንዲህ ቅልጥልጥ ብሎ እንጂ! በተራ ጆሮዎች በኩል አሚልጮ ለመባት እንዲያስችል !!"*

ቅልጥልጥ ያለን ውሸት ነጋ ጠባ እየደገሙ፤ስደት ለወሬ ያመቻልና ነፍሰ ገዳዮቹ ሰለባ ነን ብለው እየለፈፉ፤ትላንት የወጉትን ወይም ሲታገል ቅንጣት ድጋፍ ያለሰጡትን ዛሬም ዓይናቸውን በጨው አጥበው ሲዘምቱበት ማየታችንን በኢሕአፓ ላይ እየደረሰ ያለው የሀሰት ናዳ ምስክር ይሆናል ። ወያኔ ስልጣኑን ለመጠበቅ ያሰጋኛል ብሎ ከልብ የሚፈራውን ድርጅት ባገኘው ቀዳዳ ሁሉ ለማጥቃት መነሳቱ የሚጠበቅ ሲሆን ይህን ዘመቻ አጅበው በድርጅቱ ላይ መሠረተ ቢስ ክሶችንና አሳፋሪ ውሸቶችን የሚረጩት ግን በጥብቅ መወገዝ ያለባቸው ናቸው ። ኢሕአፓ የኢርትራን መገነጠል ወይ ነጻ መሆን አልቀበል ብሎ ከሻዕቢያ መጣላቱና በዚህም መጎዳቱን ደግሞ ደግግሞ የገለጸ ሲሆን በመሰረቱ

የዚህን ትክክልነት ኢሳያስ አፈወርቂ ሳይቀር አረጋግጦታል ። ለዚህም ነው ድርጅቱ ኤርትራን አስገነጠለ የሚለው ክስ ከንቱ ሆኖ 'ትል የሞላው ቋንጣ ሆኖ አሁንም ሊለፍፉት የሚጥሩ ማፈሪያዎችን መስማቱ የሚያንገሸግሽ የሆነው ። በቅርቡ ጊዘ ወደ አሜሪካ ተጉዞ በዚያ ትውልድና በኢሕአፓ ላይ ጸያፍ ዘመቻ የከፈተው የቆሻሻ ታሪክ ባለቤት ፕሮፌሰር እንጂ ደርግ 60 ዎቹ ላይ ላደረሰው ግድያ  ኢሕአፓ ተጠያቂ ሊሆን አይችልም ። የአሜሪካ መሳሪያ ሆኖ አልተገኘም ። የደርግ ኢሰፓ ባለስልጣን ሆኖ ግፍ በሕዝብ ላይ አልፈጸመም ። በአሶሳ ሻዕቢያና ኦነግ አማራውን ሲገድሉ ዝም አላለም፤ አወገዘ አጋለጠ እንጂ ።  በከተማ በገጠር ደሙን ለሀገሩ አፈሰሰ እንጂ በደርግ ለነጻ ትምህርት በየኩባና ምስራቅ አውሮጳ አልተላከም ። ኢሕአፓ ለሀቅ ቆመ እንጂ በረ ወለደ፤ በመውለድ ላይ ነው ይወልዳልም ከሚሉ ነፍሰ ገዳዮችና አረመኔ አገዛዞች ጋር አልሰመረም፤አላበረም ። ምናልባትም ይህ ይሆናል አላቋርጥ ላለው የሀሰት ዘመቻ ምክንያት የሆነው ።

ይቀጥላል